SYNOD

# ቤተክርስቲያናችንን እናድን
# መስጊዳችንንም!

እስቲ እግዚኦ እንበል!

ከኮማንደር አሰፋ ሰይፉ
ጥር ፫ ቀን ፪ሺ፡ህ ፫ ዓ ም

*"ለሲኖዶሶች መስማማያና ከሙስሊሞች መተባበሪያ ቀና ሀሳብ!"*

*አጭር መግቢያና ማሳሰቢያ፦*

*ማሳሰቢያውን ላስቅድም፣*

*ጌታችንን መድሃኒታችንን በማቴዎስ ወንጌል ም፲፦ ቁ ፲፯ ላይ፦ አንዱ "ቸር መምሕር ሆይ…" ብሎ ጥያቄውን ሲጀምር፦ ጌታም ሲመልስ ቁ ፲፰ ላይ "ስለምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ቸር ማንም የለም።" ያለውን፦ደግሞም ማቴዎስ ም 23ን ከመጀመሪያው እንድታነብቡ ስጋብዝ ለመንሰኤዬ ቁ፯ ላይ "በምኩራብም …መምሕር ሆይ፦ መምሕር ሆይ፦ ተብለው እንዲጠሩ ይወድዳሉ።እናንተ ግን መምሕር ተብላችሁ አትጠሩ።መምሕራችሁ አንድ ስለኾነ እናንተም ኹላችሁ ወንድማማቾች ናችሁ።…ሊቃችሁ አንድ እርሱም ክርስቶስ ነውና ሊቃውንት ተብላችሁ አትጠሩ።…"እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ምክሮች/ትምሕርቶች ብዙዎች ናቸው።ለዚህ ዋናው ደግሞ፦ ወገን እንዳይሳሳትብኝ የምፈልገውና የምለምነው ቁ ፱ ላይ "* ***አባታችሁ አንዱ እርሱም የሰማዩ ነውና፦ በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ አትጥሩ።"*** *በተለይ የተጠቀሱት፡- የጌታችን የመድኃኒታችን ቀጥታ ትዕዛዛት ስለኾኑ፡- ለኔ ይግባኝ የሌላቸው ናቸው።*
*ስለዚህም ከንግዲህ ወዲህ ማንንም በጽሑፍም ኾነ በንግግር ብፁእ ወይም ቅዱስ እንዲሁም አባት አልልም። ብዬ የነበረውን ለማስማማት ስል አንደዬ አፈረስሁት። እመለስበታለሁ።*
*ኾኖም መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ሰፊ ስለኾነ ልታረም የምችልበት አንቀጽ ካለ ያስተምሩኝ ዘንድ ለአንባቢያን ኹሉ ጥያቄዬን አቅርቤ ነበር። ይኸ የኾነው ከ፲፱ ዓመታት በፊት በጻፍሁት መጽሄት ዓይነት ላይ ነበር ። በአንዳንድ የ፪ቱም የሲኖዶሶቹ አባላት እጅ ገብቶ እንደነበረም ተነግሮኛል። አንድ ብፁዕ/ቅዱስ ስለሚባለው የተነገረኝ "እኔ ቅዱስ እንደኾንሁ እናንተም ቅዱሳን ኹኑ" የሚል መነሻና መድረሻ የሌለው ነገር ነበር ፦ ይህም ቢኾን ቅዱስ መኾንንና ቅዱስ መባልን ያምታታ ስለነበር አልተቀበልሁትም።*

*እኹንም ቢኾን የተጠቀሰውን የጌታ ትእዛዝ የሚያፈርስ ካገኘሁ ልማር ዝግጁ ነኝ። የማንንም ክብር ለመንካት አልፈልግምና! እንዲህ ለመባለግ፣ እድገቴ፦- ትምሕርቴ፦ ባሕሌ፦ እድሜዬና የሥራ ሞያዬም አይፈቅዱልኝ። ስለዚህ ፓትሪአርኩንም ኾነ፦ ጳጳስ - ሊቀ ጳጳሳትን በቀና እንዲረዱልኝ ስለምን አደራዬ ጥብቅ ነው።*

አኹን መግቢያውን ላስከትል።

በ፲፱፻፷፮/፷፯ ከዚያም በኋላ ነገራትን በውል ለማገናዘብ ዕድሜ ላልፈቀደላችሁ፦በስደትና ሌላም ምክንያት ሊያተምሯችሁ ከሚችሉት የተራራቃችሁ፦ ከዚያም በኋላ ስለዘውድ ግዛት ቀና ነገር መናገር በማይቻልበትም ኹናቴ ላደጋችሁ ልጆቼ አንዳንድ መሠረታዊ ቁምነገሮችን ማስጨበጥ የዕድሜ ግዴታ አለብኝ። ለአገርና ለወገን ላለመቆም :- ብትሸሹም ልታመልጡት የማትችሉት:- ሀላፊነት አለባችሁና!

በረጅሙ የዘውድ ዘመናት ኢትዮጵያ በውስጥዋ ካሉት ሕዝቧ ጋር የነበራት ትስስር የእናትና የልጅ ነበር:- ይህም

“ሞቼ ተነስቼ ልሙት እንደገና፥
ላገር(ለናት) አንዴ መሞት አይበቃትምና!”

በሚል ዕምነት ለአገር ለወገን መሠዋትን በታላቅ ክብርነት በመውሰድ አገራቸውን ሳያስደፍሩ፦ ክብርዋን በዓለም ውስጥ በብቸኛነት ይጠብቁላት ነበር። ደርግ ሲመጣና አንዱን ባለዘውድ በ፻፷ ባለዘውዶች ሲለውጥ ደርግን የሚቃወምና ለመቃወምም የሚያስብ ኹሉ “ዘውድ በኪሱ ይይዛል”” ይባል ነበር።

ያኹኖቹ ሲመጡ ደግሞ “ፓርቲ! ፓርቲ!” ተብሎ “ሞቼ ተነስቼ ልሙት እንደገና…” የሚባለው መቅረቱን በኢሳት ቴሌ ቪዝን ቃለ ምልልስ ላይ (እግዚአብሔር ይስጣቸው፦ እኛም እንርዳቸውና!) ባስተላለፉልኝ ጊዜ ብዙሓን ወጣቶች ብዙ ልብ የሚነኩ አስተያየታቸውን አካፍለውኛል። አንዱን ባጋራችሁ፦ “ታዲያ እናንተ መቼ አስተማራችሁን?!” የሚል የንዴትና የቁጭት ትችታቸው (ለመጀመሪያ ጊዜ ያልኾነ) ተደጋግሞል/ብኛል።

በቤተክርስቲያናችንም ጉዳይ ግዴታና ሃላፊነቱ የኹላችንም በይበልጥ ግን ከዘውድ በኋላ በተወለዱትና ባደጉት ላይ ስለኾነና ስለሚኾን አንዳንድ የማውቀውን የማካፈል ግዴታ አለብኝ።

“ግዴታና ሃላፊነቱ የኹላችንም ነው።” ስል በዋቢ ላጠንክረው።ለአገራዊ መስተዳድር የበላዩ ሕግ (በማን አለብኝነት! ከሚገዙት በስተቀር) “ሕገ መንግሥት” የሚባለው ሰነድ ሲኾን። ለቤተክርስቲያናችንም እንደ ሕገ መንግሥት ሲያገለግል የኖረው፦ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትነት “ፍትሐነገሥት” ነው።
ከዘውድ በኋላ ግን በምድራዊያን ገዥዎች ደፋርነትና (ድንቁርናና ፍቅረ-ሥልጣን!) በመንፈሳዊ መሪዎችም ተባባሪነት እስከተደፈጠጠ ድረስ፦ የበላይ

ሕጓ “ፍትሐ ነገሥት።” ነቱ በስም ብቻ ቆይቷል። በተለይም ፓትሪአርክን በመምረጥ ረገድ።

ፍትሐ ነገሥት ሃይማኖትን የማስፋፋት ሃላፊነት ለካህናት ሲሰጥ፦(ትምሕርቱና ዕውቀቱ ስላላቸው) ሃይማኖትን የመጠበቅ ግዴታን በምእመናን ላይ ጥሏል። ብዛት ኃይል ነውና!

ግዴታችንን ካስጨበጥሁ፦ የቤተ ክርስቲያናችንን የቅርቡን ታሪክ ቀንጨብ አድርጌ ላቃምስ። ጭብጤን ለማስረዳት ያህል እንዲረዳ።

የቤተክርስቲያናችን አስተዳደር ከግብጾች ወደ ኢትዮጵያውያን አስተዳደር ሙሉ በሙሉ  የዞረው በ.ቀ.ኃ.ሥ ዘመነ መንግሥት በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም. ነበር። በትግል! የመጀመሪያውም ፓትሪአርካችን አባ ባስሊዎስ በጣም የተከበሩና የተውደዱ እንደነበሩ አይቻለሁ ሰምቻለሁ። ለዚሁ ተከባሪነታቸውና ተወዳጅነታቸው ከሚነገርላቸው አንዱን ለወጣት ላካፍል። የ፲፱፻፶፫ቱ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ በሚኪያሄድበት ወቅት ዕውነትም “ቅዱስ” ሊባሉ የሚገባቸው ፓትሪአርክ በሚታኮሱት ወንድማማቾች፦ የክብር ዘበኛና የጦር ሠራዊት፦ መካከል እየተመላለሱ ተኩሱ እንዲቆም አድርገዋል። በዚያን ጊዜ (በጉርምስና) አዲስ አበባ ውስጥ ያለውን እንቅስቃሴ እየተዘዋወርሁ ሳይ ከቅዱስ ፓትሪአርኩና ከአሜሪካን አምባሳደር መኪናዎች በስተቀር አንድም ሌላ አለማየቴን አረጋግጣለሁ። (ይኸውም ማክሰኞ ለረቡ አጥቢያ ተጀምሮ፦ሐሙስ ከሰአት በኋላ ትንሽ ተኩስ ተሰምቶ፦ ሌሊቱን ደምቆ ዓርብ ጠዋት ከ፫ ሰዓት እስከ ፮-፯ ስላየሁት ነው)  ፓትሪአርኩ ይኸን ሲያደርጉ ግን ከብራዚል ወደአገራቸው በመመልስ ላይ ከነበሩት ቀ.ኃ.ሥ ጋር እየተነጋገሩ ለክብር ዘበኞች አማጺያን ምሕረት እንዲደረግላቸው ቃል አግኝተው እንደነበር ለኹኔታው ቅርብ ከነበሩ ተረድቻለሁ። ቀ.ኃ.ሥ ኢትዮጵያ እንደተመለሱ ሌ.ኮሎ ወርቅነህ ገበየሁንና ሌሎች ኹለት (?) በስቅላት እንዲቀጡ አዘዙ።

ይህን የሰሙት ቅ.ፓትሪአርክ ‘ቃል ፈረሰብኝ፡፤ እኔንም ቃለአባይ አደረጉኝ!’  ብለው ደብረ ሊባኖስ ገዳማቸው ገቡ። ፓትሪአርክም ቢኾኑ መነኩሴ ናቸው፦የመነኩሴ መግቢያውም ገዳም ነውና!

ከን.ነገሥቱ ቢላክባቸውም እምቢ ብለው በኋላ በአማላጅ ሲመለሱ ከመንግሥት ግልበጣው መሪ በስተቀር፦ ያውም በፍርድ፤- የሌሎቹን የሞት ቅጣት ወደ እስር እንለውጥላቸዋለን ተብለው ፦ ምክንያቱም የብዙሐንን ንጹሕ ደም አፍስሰዋል፦ ሕይወትም አጥፍተዋልና!’ ተብለውነው ወደ መንበራቸው የተመለሱ።

በዘመናችን እንኳን ፓትሪአርክ ጳጳሳትስ ኹሉ መነኮሳት ናቸውን  የሚያስብሉ ብዙ ኹናቴዎች ተፈጥረዋል። አንዱን ብቻ ለአብነት ያህል ላቅርብ። ሟቹ ኢሕጋዊው ፫ኛው ፓትሪአርክ ሎንዶንን ሊጎበኙ ሲመጡ የገጠማቸው ተቃውሞ ለአያሌ ዘመናት የተለያዩ ተቃውሞን ላስተናገዱት የሎንዶን ፖሊሶች አዲስ ኾኖባቸው ነበር። ከ፩ ፖሊስ ጣቢያዎችና ከ፪ ፈጥኖ ደራሽ ምድቦች (ቴሪቶሪአል ግሩፕ - አዛዡ እንደነገሩኝ) በመጣ ኃይል እንኳን መቆጣጠር ተቸግረው ነበር። ደግሞ እንደተጨመረልኝ “እንዲህ ዓይነት ቁጣና ንዴት ገጥሞን አያውቅም!”

ነበር።" ዕውኑ ይህ ሲኾን የኀብኘው  ቃል አቀባይ፦ አብረውም የቁጣው ቀማሽ የነበሩ ኢትዮ ቴ.ቪ.ዝን ላይ "ተቃውሞው የተጋነነ ነው እንጂ ይህን ያህል አልነበረም።" በማለት በቢቢሲ ሬዲዮ የተላለፍውን መግለጫ ጭምር ለማስተባበል ሞከሩ።

በቦታውና በጊዜው የዓይን ምስክር የነበረው ክ. አቶ ንጉሤ ፍትህ-ዐወቅ የከፍተኛ ፍ/ቤት ፕሬዜዳንት የነበረና የክ. ፕሮፌስር አሥራት ጠበቃና ባልንጀራ የነገረውንም ለማስተባበል ሲሞክሩ ጳጳሱ

"እንዲያው እኮ እዚህ ግቡ የማይባሉ አልባሌዎች ናቸው!" በማለት በውሸት ላይ ስድብ ሲጨምሩ ፦ ኹለዬም ዕውነተኛና ቀጥተኛ የነበረው ክ. ፕሮ አሥራት፡- የሚያውቀንን ወንድሞቹን ሊያዋርዱ ሲሞክሩ

"መነኩሴ ይዋሻል እንዴ?!" ሲል አግርሞቱን ለጋዜጥኛ ይወረውራል። ይኽን የሰሙት ጳጳስ

"እኛ ጳጳሶች ነን። መነኩሴዎች አይደለንም!" ይላሉ

ይችን ያገኘ ጋዜጠኛ ወደ ፕሮፌሰሩ ሄዶ ይኽንኑ ይነግረዋል።
አሥራት ወልደየስም በተለምዶው የሞቀ ሳቁ አሳጅቦ፡-

" ይቅርታ! - ይቅርታ! - ስህተቱ የኔ ነው። እኔ እኮ ጳጳስ መነኩሴ መስሎኝ ነበር!!" ብሎ ዘጋው።

ልጆቼ ሆይ፡- ይኽን ዕውነታ ሳቀርበው አንጀቴ እያረረ ነው። እንኳን ጳጳሶቼ - ሊ. ጳጳሶቼ ተራ መነኩሴዎቼም ቢኾኑ በዚህ ዓይነት ሲጠሩ/ሲነሱ ያምመኛል። ያነሳሁት ከንግዲህ እንኳን ቢቆጠቡልኝ ብዬ ነው። ውርደታቸው ውርደቴ ነውና! በዚሁ ምክንያት የሚቹን  የ፳ኛውን ኢሕጋዊው ያሏቸውን የባሱትን አልፋለሁ።

ደርግ ሲመጣ ፪ኛውን ፓትሪአርክ "በፈቃድዎ መንበሬን ለቅቄአለሁ ይበሉና ፳ሺህ ብር ደመወዝ፡ ግሩም መኖሪያ ቤት፡- አዲስ ላንድ/ሬንጅ ሮቨር ከነነጅውና ቤንዚኑ ሌላም የሚያስፈልግዎትን ኹሉ እናሟላልዎታለን። አሊያም የፈለጉበት ገዳም ሊገቡ ይችላሉ!" ቢሏቸው።
ከአቅሜ በላይ የኾነ ነገር ጠየቃችሁኝ፡- የኔ ያልኾነውን ለመስጠትም ኾነ ለመልቀቅ እንዴት እችላለሁ። መንበሬን በመሃላ ስቀበል ፍትሐነገስቱንና የቤት ክርስቲያናችንን ቀኖና አክብሬ ለማስከበር ነው። ብታመም እንኳን ሲኖዶሱ በእንደራሴዬ ያስተዳድራል እንጂ በሕይወት እያለሁ ሌላ ሊተካ አይችልም። ብለው በዕምነታቸው በመጽናታቸው በቃላቸውም በመርጋታቸው ሃይማኖትን፡- ቃልንና ክብርን የማያውቀው ደርግ ለመስዋትነት ዳረጋቸው፤፡ በክፉ ጭካኔና ስቃይ።

ስለዚሁ ጉዳይ የውጪው ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ "የቋሚ ምስክርነት" በሚለው መጽሐፋቸው ሲመሰክሩ

" ምንም በእሥር ላይ ኾነው ቃላቸው ባይሰማም አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ፓትሪያርክ እኔ ነኝ እያሉ ይጮሁ ነበር። ደርግ በማያገባው ገብቶ "በፈቃዴ ፓትሪያርክነቱን ለቅቄያለሁ ይበሉና ሙሉ ቀለብዎን፡- አንድ ቪላ ሰጥተን

በክብር እናስቀምጥዎታለን “ ሲሉ በማታለል ቃል መላልሰው ጠይቀዋቸው ነበር። ነገር ግን አቡነ ቴዎፍሎስ ሊታለሉላቸው አልቻሉም።...” ገጽ ፸ ስለመደብደባቸውና መስቃየታቸው በኋላም መገደላቸው ጽፈዋል። ይህን ያስገባሁት ወገን በማነጻጸር ግንዛቤውን ያዳብር ዘንድ ነው።

በቦታቸውም (እንደሰማሁት) አንድ ከፖለቲካ የነጹ ጥሩ መነኩሴ አስቀመጠ። በዚህ ጊዜ ሌሎች የኦርቶዶቅስ ቤተክርስቲያን መሪዎች ለኢትዮጵያዊው ፭ኛ ፓትሪአርክ ዕውቅና ነፈጓቸው። “ፓትሪአርክ እያለ ሌላ አይሾምምና!”

ያኹኑ ገዥዎች ሲገቡ ልክ እንደደርግ ፬ኛውን ፓትሪአርክ እንዲለቅቁ አዘዙ። ለሰላም ስል፡- ጉዳዩም የቅርብ ጊዜ ስለኾነ፡- ዝርዝሩን አልፈዋለሁ። ግን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶቅስ ተዋህዶ መከፋፈል ዓይነተኛ ጠንቅ መጣሉን አስጨብጬ ዝርዝሩን እመለስበታለሁ። ከዚያ በፊት ግን ሌሎች የቤተክርስቲያን እህቶቻችን ትመሳሳይ ዕቀባ አለማድረጋቸውን ማስጨበጥ እፈልጋለሁ።

ያኹኑ ገዥዎች የመከፋፈያ ሕገ መንግሥት ተብዬውን ጸደቀ ብለው ግብዣው ሲንጃጃ፡- ከ አርቃቂዎቹ ጋር በቅርብ ኾኖ ይሠራ የነበረ አንድ ሰው የሚያስደነግጥ ነገር ይሰማል። ከኋላው አራት የትላልቅ አገሮች አምባሳደሮች ሲነጋገሩ ነው። እንዲህ ነበር፡-

አንዱ - በዚህ ሰነድ ኢትዮጵያን ቁጥጥራችን ውስጥ አስገባን አይደል?

ኹለተኛው - አይ! ገና ነን።
አንደኛው - ምን ይቀረናል?
ሦስተኛው - አክራሪ እስላሞችን ማስገባት!
አራተኛው - ጥሩ ብለሀል። ግን አኹንም የሚቀር አለ።
አንደኛው - ከዚህ በላይ ምን ልንጨምር እንችላለን?
አራተኛው - የኢትዮጵያ ኦርቶዶቅስ ቤተክርስቲያንን በወንጌለኞች መበረዝ!!!(የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ተከታዮች አማኞች ለኢትዮጵያ መቆማቸው ዕውቅና እሙን ስለኾነ አዲሶቹን ለነርሱ ጥቅም ለማዋል ምቹ እናደርጋቸዋለን ሲኾን፡- የዚህ ጸሐፊ እምነት ግን መሠረታቸው ተዋህዶ ኾኖ በተለያየ(ዩ) ምክንያት(ቶች) ቢለዩም የአገር/ለአገር ያላቸው አቅዋም ይለያል የሚል እምነት ፈጽሞ የለውም)

ኹሉም ተስማሙ! ኢትዮጵያን ቁጥጥራቸው ውስጥ ለማስገባት ! ! !

እንግዲህ ያገር ልጆች፡- እስላም ክርስቲያኑ፡- ምን እያየን ነው? ከአንድ ወር ያህል በፊት በአሜርካን ድምጽ ሬዲዮ የሲኖዶሶችን ዕርቅ በተመለከተ የመፍትሄ ሀሳብ ሳቀርብ ከቤተክርስቲያናችን በተለያዩ ወንጌላውያን ስም የሄዱብንን ቁጥር ከአራት ሚሊዮን በላይ አድርጌው ነበር። ይሄን ጉዳይ በቅርብ የሚከታተል ወዳጄ ከነሱ፡- ከወንጌላውያን አሃዞች፡- ያገኘውን መሠረት አድርጎ ግምቴን አስተካከለልኝ። ከአስራ ስምንት ሚሊዮን አዎን ከ18 000 000 በላይ ነው ! ! ! ፍትሐነገሥቱ ኹለት ፓትሪአርኮች ቢኖሩ “ ቤተክርስቲያን ትደኸያለች!!!” ያለውን ሳያውቁ ቀርተው ነው ሲኖዶሶቹ የተከፋፈሉት? ባሉበትም የሚቀጥሉት?
ይሄው ጸሐፊ፡- በመስከረም 1993 ዓም.፡- የውጪው ሲኖዶስ ኦሃዮ ርክበ ካህናት በሚያደርግበት ጊዜ እንድገኝ ያመቻቹልኝ ዘንድ አስተማሪዬ የነበሩትን የውጭውን ሲኖዶስ

ዋና ጸሐፊ በስልክ ጠይቄ ፭ኛው ፓትሪአርክን ለንደን ከማስተናገድ ጋር ስሜን ሰምተው ኖረው፡- በምረቃ "ስብሰባው የካህናት ብቻ ቢኾንም፡- አንተን እንቀበልሃለን" ብለው ሄድሁ። እኔም 'ቅዱስ - ብፁዕ - በሚባሉት ቃላት በጽሑፍም በንግግርም አልጠቀምም ያልሁትን ለዛሬው ሳነሳ እንደንስህ መናዘዜን "የተናገሩት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ!'ን መግቢያ አድርጌ በቃላቱም ተጠቅሜ ስንደቅ ዓላማዬን ትከሻዬ ላይ በማድረግ ተንበርክኬ በውጪ የቤተክርስቲያናችን ልጆች በመቆሪዮስ -( በይስሐቅ በቀኃሥ ለምዕራቡ ዓለም ሊ.ጳጳስነት የተሾሙት፡-) በጳውሎስ እና ማንኛችሁንም በማይፈልጉ ለአራት የተከፍልን ስንኾን አገር ውስጥ ያለው ችግር የገጠር ቤተክርስቲያኖችን ግድግዳቸው የዘመመባቸው ለማቅናት፡- ጣሪያቸው የሚያፈስስባቸው ለመከደን ብቻ ሳይኾን ቅዱስ ቁርባንን ለመፈተቻ እንኳን ባለመቻላቸው እየተዘጉ መኾናቸውን፡- ካህናት ሳይቀሩም በጴንጠዎችና በጆሆቫዎች እየተወሰዱብን መራቆታችንን፡- ውጪ ያለነውን ቢያስተባብሩ ግን ይህን ኹሉ መቋቋም መቻላችንን በማስረዳት ብለምን አልኾነልኝም። በመንበርከኬ ብዙ ተጨንቀው እጆቻቸውን ከፍ ዝቅ እያደረጉ እንድነሳ የሞከሩትን የሲኖዶሱን ዋና ጸሐፊና የርዕሰ አድባራቱንም አለቃ ኹለዬ በአክብሮት አስባቸውለሁ። እኔ የተንበረከክሁት ለሰው ልጅ መንበርከኬን ጌታዬ እንደሚከለክለኝ አጥቼው ሳይኾን ሌሎቹ ችግሬን/ችግራችንን ተረድተው ይረግቡ እንደኾን በማለት ነበር። ከምኻከላቸው አለ ሲኖዶሱ ጸሐፊ በዕድሜ (ሌላውን እንተወውና) ከኔ የሚቀርብ አልነበረም። "የአረጋውያንን ገጽ አክብር!" እያሉስ ያስተምሩን አልነበረም? አልፎም ከመጽሐፍ ጠቅሰው 'ለኛማ አትንበርከክ! ብለው ያስተምሩኛልም ብዬ ነበር። ለምሳሌ ዮሐንስ ራዕይ ም19 ከ ቁ 9 ጀምራችሁ ብታነብቡ ቁ 10 "ልሰግድለትም በእግሩ ፊት ተድፋሁ። ርሱም፡- እንዳታደርገው፡- ተጠንቀቅ፡-ካንተ ጋር የኢየሱስም ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ።ለእግዚአብሔር ስገድ ..." ተረሳ! ልመናዬ ተሰምቶልኝ ቢኾን ያኹኑን አደጋ ባናስቀረው እንኳን አንቀንሰውም ነበር??

ለመኾኑ ሲኖዶሱ ፬ኛው አምሞኛል። በመንበሬ ሌላ አኑሩበት ሲሉ፡- "አይኾንም! አይቻልም! ይሄማ ቤተክርስትያናችንን ያደኸይብናል፡ ፍትሐነገሥቱም ይከለክላል ያለ ነበር?" አፌን ሞልቼ በፍጹም። ሊ.ጳጳሳት መልከጼደቅና ኤሊያስም ቢኾኑ በዕለቱ አልነበረም። ለማንኛውም ሲኖዶሱ ሕግ ሲጣስ ተባበረ እንጂ አልተቋቋመም። የገዥዎቹ ተጽእኖ ነበር? አለጥርጥር! ግን ተጽእኖውን ለመቋቃም የተደረገ ነገር፡ የተወሰደ ርምጃ ነብር? አልታየም አልተሰማም። ስለዚህ ሲኖዶሱ ከገዥዎቹ በማበር ለቤተክርስቲያናችን መደፈር ብሎም መዳከም የተጫወተው ሚና ቀላል ነው ማለት ይቻላል?

በሲኖዶሱ ላይ ጣታችንን ስንቀስር ምእመናንስ? ጥቂት ውጪ ካለነው በስተቀር፡ ምን አደረግን? ርግጥ ፍትሐነግሥት ስለጣለብን ሃላፊነት አላስተማሩንም ማለት እንችል ይኾናል። የተፈጥሮ ዕውቅትስ ቦታ የለውም? አይመስለኝም። ከወቀሳም አንድን። ከሃላፊነትም አናመልጥ።

፬ኛው ሲወጡ አድራጎታቸው ትክክል ነው በማለት ደጋፊዎቻቸው የክርስቶስን መሰደድ እንዲሁም የአንድ የኮፕት ፓትሪአርክንም መሰደድ በማቅረብ አላዋቂዎችን አሳስተዋል! የሚል እምነት አለኝ። የክርስቶስን ከዚህ ጋር ማመሳሰል ይገባል? የኮፕቱስ ቢኾን ከኛ ጋር ተመሳሳይነቱ እምን ላይ ነው? በእኛ ላይ የተጫኑት ገዥዎች እንገደል አላሉ። ሰፊ ምርጫ ሰጡ እንጂ። ታዲያ ስደት ከተመረጠ መጀመሪያ የነበሩበት ኬንያ ተሰድዶ የነበረውን ወገን መርዳት ማጽናናት የበለጠ ኃይማኖታዊ አይኾንም ነበር? የሚሉ ወገኖች ጥቂት አለመኾናቸውን ማጤኑ አይጎዳም። ስለዚህ የውጭውም ሲኖዶስና ተባባሪዎቻቸው

ዕውነታውን በጭቁኗ የኢትዮጵያ ኦርቶዶቅስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ልጅነትና በኢትዮጵያዊነት ሲመዝኑት ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንና አገሪቱ የሚጠቅም ሥራ ሠርተናል ይላሉ? ለዚህ እግዚአብሔርን ዳኛ ኅሊናቸውን ምስክር ያድርጉ።

በአንጻሩ ወንጌላውያን ምን አደረጉ? በጎረቤት አገሮች ላሉት ወገኖቻችን ብቻ ሳይኾን በሊባኖስና በሴቶች ልጆቻችን ላይ ለመስማት የሚሰቅቅ ወንጀሎች በሚፈጸሙባቸው አረብ አገሮች ደረሱላቸው፤፡ ርዳታቸውን፡- ማጽናናታቸውን ትምሕርታቸውን አደረሱላቸው። በሬዲዮንና በቴ.ቪ ማጽናናታቸውን ማስተማራቸውን ቀጠሉ። እኛ ግን ከሊቅ እስከደቂቅ ርስ-በርስ መናቆርን መርጠን ቤተክርስቲያናችንን አራቆትን። ይህን ስል ፓትሪአርኮችን፡- ጳጳሳትን፡- መነኮሳትንና ካህናትን ብቻ ሳይኾን ውጪም ውስጥም፡- በተለይም ውጪ ያለነውን ምእመናን፡-ከወቀሳ ሳናሸሽ ነው። መድረሻ የለንምና! ኅሊናችንን እንመርምር።

ለመኾኑ በመጨረሻ ጊዜ ለፍርድ ሲመጣ “ ታርዤ አለበሳችሁኝ...” ሲል የእኛ መልስ ምን ሊኾን ነው? ርስ-በርሳችን እኮ ለሥልጣን ብለን እየተባላን ነበርን!” ያዋጣል? ወደ ልቦናችን እንመለስ፡- የኅሊናችንንም ወቀሳ እንስማ!

እስቲ ኢ.አ ላይ ያለው ሲኖዶስ በ፭ኛው ፓትሪአርክ ዘመን ግዳጃቸውን ተወጥተናል ብለው ያስቡ እንደኾን?

--- አክራሪ ሙስሊሞች/ብሔረተኞች አርሲ ውስጥ የሃይማኖት መንጋቸውን ሲያተራምሱና ወንዶቹን በማንጅራታቸው ሲያርዱ፡- ርጉዞቹን ቀድደው ሽሎቻቸውን ሲጥሉባቸው ምን አሉ? ምንስ አደረጉ?

--- የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በታጠቁ ፖሊሶች/ወተደሮች ሲታደኑ ፓትሪአርኩ ጊቢ ገብተው የሙጥኝ ሲሉ ባለሥልጣኑም ፖሊስ ጠርተው “እዚህ አሉላችሁ!” ብለው ለአባራሪዎቻቸው አሳልፈው ሲሰጡ ምን አሉ? ምንስ አደረጉ? የዘመን ገደብ የሌስው የቤትክርስቲያናችን ክብር ተገፈፈ! ልጆቻችንን ላሳዳጆቻቸው አሳልፈን ለምን ሰጠን? አሉ? አልተሰማም።

--- ወንድ ወጥቷቸው የኢሕጋዊውን ፓትሪአርክ ሙስና - ያስተዳደር በደል - ወገናዊነት ወዘተ የሚመረምር ጉባኤ ሰይመው ጉባኤዉም በቆራጥነትና በቃል ኪዳን አክባሪነት በሚገባ መርምሮ ለሲኖዶስ ሊያቀርብ ሲል አጥኚዎቹን ሊ. ጳጳሳት ከመኖሪያቸው ፖሊሶች በር እየገለበጡ ሲያጉሏሏቸው ምን አደረጉ? እኛው ያዘዝናቸው ወንድሞቻችንን ለእንዲህ ዓይነት ውርደትና ስቃይ ዳረግናቸው! ምድራዊ ኃይል ባይኖረንም ለኃያሉ ለሰማዩ ጌታ አቤት እንበል አሉ? “ርሱማ ተረስቶ!” የሚል ድምጽ ከየት ነው የሚሰማኝ??

--- ይህ እንደኾነ ድሬዳዋ ላይ አንድ የግንባታ ጨረታ ወጥቶ በሲሶ እሠራዋለሁ ብሎ የቀረበውን አስቀርተው በኹለት እጅ እጥፍ ለበለጠው መሰጠቱን ጋዜጣ ሲያወጣ ምን አደረጉ? አሉ?

--- የጋዜጣን ካነሳሁ፡- ቅ. እስጢፋኖስ ውስጥ ስልተገደሉት ባህታዊ አንድ ጋዜጣ የመጀመሪያውን ጥይት የተኮሱት ፓትሪአርኩ ናቸው። ለዚሁም ፲፪ የዓይን ምስክሮች አሉኝ ሲል “ነፍሰ-ገዳይ ፓትሪአርክ ያዉም ቤተክርስቲያናችን ውስጥ!?” ያላችሁ አላችሁ? እንደተለመደው . ጭጭ - ምን ጭጭ...

--- ኢሕጋዊው ፓትሪአርክ “ተጠሪነቴ ለሲኖዶስ አይደለም ሲኖዶስ ለእኔ ነው እንጂ!”

ሲሉ ምን አደረጉ? ለሲኖዶሱ ሥልጣን በአንድ ቆሙ? አልተሰማም። ማጉመትመት ግን እንደነበር አይካድም። የባለ ሥልጣኖች ድምጽ/ክንድም ሲታይ ግን ከሰመ። ሲኖዶሱም ድረሱልኝ አላለ፡- መእመናንም ኾኑ ውጪ ያሉት ሲኖዶስ "እንዴት?!" ሲል ይህ ጸሐፊ መስማቱን አያስታውስም። ምን ዓይነት ተላላነት ነው? ውስጥ ባለው ሲኖዶስ

የፓትሪአርኩና የሲኖዶሱ አሳዛኝ ግድፈቶች ተነግረው ስለማያልቁ ኢሕጋዊው ፓትሪአርክ ሮማ ሄደው ከሮማው ፓፓ ጋር በአንድ መቀደሳቸው ሃይሞኖታዊ ሕጸጽ ሲኾን አንዳችሁ እንኳን ሳትተነፍሱ፡- ነፍሳቸውን ይማርና የሊቃውንት ጉባኤ ሊ.መንበር የነበሩት ምስጉኑ አለቃ አያሌው ሲያውግዙ የት ነበራችሁ?ለምንስ አብራችኋቸው አልቆማችሁም?

ውግዘት ከተነሳ፡- ፍትሐነገሥቱ ' ከተወገዘ ጋር የተነጋገረ ውጉዝ ነው ' ሲል እናንተስ ከሌሎቹ ሊሎቹ ሲኖዶሶችም ከእናንተ ጋር ብቻ ሳይኾን ከሌሎች ብዙሐን ጋር መነጋገራችሁ ምን ይባላል? ውግዘትን ማርከሳችሁ ነው? ወይስ ኹሉንም እንዲወገዝ ማድረጋችህ? ዕርቅንስ ለምን ፈራችሁ? ዋናው ጭብጥ - ጭብጡ ርሱ ከኾነ- የ፬ኛው መመለስ አለመመልስን ቅየት አድርጋችሁ በየቀኑ - ለቁጥር በማይመች ዓይነት - አቡነ ዘበሰማያት ስታስብሉን አናንተስ ትሉት የለ? ታዲያስ "… በደላችንን ይቅር በለን እኛም…." የሚለውን ታልፉታላችሁ? ከቅዳሴ በፊት ስለምታነብቡት የንሥሐ ጸሎት አላነሳም። ከቁርባን በፊት ምእመኑን - ምን ምን ትሉታላችሁ?
ይህ የሚሠራውስ በምእናን ላይ ብቻ ነው? ወይስ መርገሙ ኅብስቱን ወደ ጌታችን ቅዱስ ስጋነት ወይኑንም ክቡር ደምነት በጸሎት ትለውጡልናላችሁ ብለን በምናምናችሁም ላይ? ሲጨንቀኝና በሀሳብ ስዋጥ፡- ይቅር ይበለኝና፡- በእንግሊዝኛ "መላመድ መናናቅን ያስከትላል!" የሚል ዘይቤ አለ። ታዲያስ የኛ ጳጳሳት -ሊጳጳሳት-መነኮሳት ወካህናት እዚህ ደረጃ ወደቁብንን? በአገራችንና በቤተክርስቲያናችን ላይ የወረደው፡- የወረዱት መዓት - አሣር ለሰው አቅም እጅግ የከበዱትና የተደራረቡብን ለማቆም ይለምኑልናል የምንላቸው ስለተሳለቁብን ይኾንን? እያልኩ እጨነቃለሁ። እስቲ ከእናንተ ውስጥ እኔን "ካልከው ሙሉ በሙሉ ነፃ ነኝ።" የሚል ካለ አብሮን ይቁም።
ባዘዥኝ መሠረት ' በሙሉ ልቤ - በሙሉ ኃይሌ አምነዋለሁ፡- አከብረዋለሁ፡-ስሙን በከንቱ አልጠራም፡- …'ብላችሁ ልቤን ታሳርፉልኛላችሁ? ከኀሊናችሁ ተማከሩ። "የለመኑትም የማይነሳ የነገሩትን የማይረሳ!" ጌታ አላችሁ ብላችሁን የል? ታዲያ አልለመናችሁልንም እንበል? ወይስ ነሳን ረሳን? ከኾነስ ለምን? ንገሩና! አስተምሩና! እኛማ "የእሥራኤል ልጆች ሆይ፡-እናንተ ለኔ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?" ሲል የፍቅር መለኪያው አድርጎናል እንል ነበር። እሥራኤላውያንም ከፍቅሩ የወረዱት/ወርደው የነበሩት ለምን እንደኾነ አስተምራችሁናል። የእኛስ ቅጣት እናንተ ለርሱ ፍቅር ብላችሁ ለምድራዊው ጥቅም በሙሉ፡- ለገንዘብንም ኾነ ለሥልጣን ምውቶች ነን ብላችሁ ተዝካር ያወጣችሁት ንገሩና!
"ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህምዉደድ፡…
ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ…" የሚሉትን መሠረተ - ሕግጋት ፈጽማችሁ በእናንተ አራያነት እኛንም እንድንፈጽም ትረዱናላችሁ ብለን ነበር። ይህ ኾኗል ለማለት ማን ይችላል? ካልኾነስ?

## "ከተናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባህር መስጠም ይሻለው ነበር" (ማቴ ፲፰፥፯)

እንዲያውም በተጨማሪ ግራ የገቡኝን ላነሳሳ፡- ስመ-ጥሩው የዋልደባ ገዳም ኹላችንም የምናውቀው በደረሰብት ጊዜ፡-

- አበምኔቱ ለምን እናንተንና አለቃችሁን ትተው ለአቶ ጠ/ ሚኒስትር አመለከቱ?
- ከእናንተ ተብሎ ስለ ገዳሙ መግለጫ ሲወጣና የአበምኔቱ ልኡክ ስለመግለጫችሁ ሲጠየቁ "የእኛ ካባ ከገዳም ነው የነሱ..."ሲሉ ምንማለታቸው ነበር?
- ገዥዎቹ እንደገቡ በአዲስ ዓለም ገዳም ላይ የስርቆት/የዘረፋ ሙከራ ተደርጎ ወንጀለኞቹ በሙሉ እስከነ ሸክማቸው ሲንቀዋለሉ መያዛቸውን ቴሌ ቪዥን ተናግሮ ወንጀለኞቹ አለ ጥያቄ ሲለቀቁ ምን አደረጋችሁ?
- በቅርቡስ በጉራጌ ውስጥ ጥንታዊ ገዳም በቁፈራ ተገኝቶ በውስጡስ ከነበሩት ጥንታውያን ቅዱሳን ቅርሶች ላይ ተመሳሳይ ሙከራ ተደርጎ በተመሳሳይ ኹናቴ ሲከሽፍ ምን አደረጋችሁ?

ነገር ቢበዛ ...! ነውና ያለፈውን ለማስታወስ ያህል ከጠቃቀስን ወደዛሬውና ወደ ነገው እስቲ መለስ እንበል።

## ዕርቅ፡-

ይኽን በኹለት ብንከፍለው፡-

አንደኛውን በሲኖዶሶቹ ሊወሰን የሚችል(የአ.አበባዎቹ ለዚሁም አዛዥ አለብን ካላሉ)

ኹለተኛውን ከአ.አ. ሲኖዶስ ሥልጣን በላይ መኾኑን ብናምንና መንገድ ብንፈልግ

በሲኖዶሶቹ ሊያልቁ የሚችሉ

ሀ- ውግዘቶቹን ማንሳት በቅድሚያ

ለ- ይቅር ለእግዚአብሔር ከልብ መባባል። እግዚአብሔር የሚፈልገው ነውና! ይህ ሳይኾን ዳላስ ውስጥ አብራችሁ በመቀደሳችሁ አብራችሁም በመብላታችሁ ተጨማሪ መርገም እንዳይወርድብን በየፊናችሁም በአንድነትም ተገቢውን እንድታደርጉ በትህትና አሳስባለሁ።

አብራችሁ ማእድ ተቀምጣችሁ የልዑካኑ መሪዎች ጎን ለጎን ኾነው ስንኳን ሊነጋገሩ በበጎ አመለካከት ሳይተያዩ ምሽቱ በማለፉ የነበረውን ኹሉ ቅስም ሰብሯል። ይገባል??እንዲህ ዓይነቱ የመጨረሻው ቢኾን አይሻልም?

## የዕርቅ ጉባኤው አባላት ሆይ!

በጌታችን ትእዛዝ መሠረት ዕርቅን በመፈለግ በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ሰላምን ለመመልሰ ያረጋችሁትን ጥረት  አከብራለሁ። ግን ገና ከጅማሬው አንድ ያልገባኝ በሂደት ይገለጽልኝ ይኾናል ብዬ በተስፋ የተጠባበቅሁት ነገር ነበር። ወይ ብልጭ! ከየት መጥቶ?
፬ኛውን ፓትሪአርክ ያባረሩት ገዥዎቹ ሲኾኑ እናንተ 'መልሱ!' ብላችሁ የምትደራደሩት ከገዥዎቹ ታዛዦች ( የአ.አበባው ሲኖዶስ) ጋር ነው። እንግዲህ እንዴት ይኾናል? አባራሪዎቹ እያሉ- እንዴት ኾኖ ነው የውጪዎቹ የሚፈልጉት ተገኝቶ ዕርቅ የሚሰፍነው?? የአ.አበባው ቢፈልግ እንኳን (ይሠመርበት!) አዎን ቢፈልግ እንኳን ፬ኛውን ፓትሪአርክ ያባረሯቸው ገዥዎች እያሉ ሊቀበሉ ይችላሉ? ጠያቂዎቹም ይገርሙኛል።

እዚህ ላይ መላዬን ላካፍላችሁ። እንዲያውም እኮ ከአንድ ወር ያህል በፊት በአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ፡- ገዝዎቹ 'የአማራንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶቅስ ቤተክርስቲያንን እንዳይነሱ አድርገን

አከርካሪአቸውን ሰብረናል።” በማለት ቢደነፉም ለቤተክርስቲያናችን ከነሱ በላይ የኾነ ይግባኝ ሰሚ አላት ወደሱ አቤት እንበል ነበር ያልሁት። አልሰማችሁት ይኾን?

እንደምታውቁት ጌታ በነነዌ አዝኖ ተቆጥቶ ምሕረቱ የበዛ ጌታ ዮናስን ልኮ በሦስት ቀናት ጾም ፀሎት ከተንጠለጠለ እሳት እንዳዳናት እኛንና የእኛንም ፡- ከልብ ከተማጸንነው፡- በነዚሁ ዕለታት ሱባኤ ያድነናል። ለዚህ፡-ከልብ ከተማጸንነው፡- ሙሉ እምነት አለኝ። በደርግ ጊዜ በሙስሊም ወንድም/እህቶቻችን አነሳሽነት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሕብረት ‘እግዚኦ!’ ብሎ አልተገላገለም?። ፀሎታችን ግን ‘ምሕረትህን አውርድልን፡- መድኃኒትህን ስጠን ሳይኾን፡- “እነዚህን ብቻ አንሳልን። የፈለገው ይምጣ!” ኾነና የለመኑትን የማይነሳው መለሰ። አኹን ግን “ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤተክርስቲያን!” የሚለውን በአፍ ልማድ ማድረጋችን ቀርቶ በልብ ከልብ ይኾን ዘንድ እንደ ነነዌ በሦስት ቀናት ሱባኤ ልባችንን ሰብረን እንድንጸልይ ነው።
ደግሞስ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ብዙ ሥልጣን ሰጥቶ እንዲያስተምሩ ከላካቸው በኋላ አንድ ያቃታቸው ጉዳይ ሲገጥማቸውና ወደ ጌታ ወስደው ርሱ ሲፈውሰው፡- እኛ ለምን አልቻልንም? ብለው ሲጠይቁት መልሱን እናንተን ለማስታወስ ሳይኾን ለማያውቁት፤- “ይህ ሊኾን የሚችለው በጾምና በጸሎት ነው።”| እንዲያውም በጽሑፌ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን በጥቅስ ላለማስቀመጥ ብዙ የተጠነቀቅሁ መኾኔን ሳትመለከቱልኝ አትቀሩም ብዬ አስባለሁ። የምንፈልገውም የቀጣይ ፓትሪአርኩ ምርጫ እንደተለምዶው ‘በመንፈስ ቅዱስ ተመርጦ!’ በማለት ብቻ ሳይኾን በውኑም ለችግራችን እንኳን መንፈስ ቅዱስን እልባችን፡- እቤተክርስቲያናችን፡- አድራጎታችን ኹሉ ውስጥ እንድናስገባው ነው።

## ዕጩዎች፡-

- ኹለቱም ሲኖዶሶች እጩዎቻቸውን ያቅርቡ። አንዱ በሌላው ዕጩ ላይ ተቃዋሚነት ባይኖረው ጥሩ ይመስለኛል።
- **አንዱ ዕጩ ግን መንፈስ ቅዱስ መኾን አለበት!**
  ለመጀመሪያ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን በቤተክርስቲያናችን ጎልውና ውስጥ ተገቢ ቦታውን ሰጠነው ማለት ነው። እስካኹን በስሙ የፈለግነውን አደረግን። አኹን ግን ራሱ የፈለገውን እንዲያደርግ መኻላችን እናስገባው። በዕጩነት ይግባ!!!
- መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ ከወጣ ዕጩዎች ኹሉ ተቀባይነት አጥተዋል ማለት ስለኾነ እንደገና ሲኖዶሶቹና፡ ገዳማት ቤተክርስቲያናት እንዲሁም የፈለጉ መእመናን ጾም ይዘው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ምርጫው በአዲስ ዕጩዎች ይደገማል።
- ውጤቱ ያው ከኾነ በመንፈስ ቅዱስ ተቀባይነት ያገኘ እስቲመጣ ይደገማል/ይደጋገማል
- ለሰላም ለአንድነትና ለፍቅር ሲሉም ፬ኛው ፓትሪአርክ ስማቸው በዕጩነት እንዲገባ ይስማማሉ፡- ለውጤቱም ይገዛሉ። ይህ ከኾነ ኹለት ሲኖዶሶች የሚባለውን ችግር ቀበርነው ማለት ነው። ይህም ፬ኛውን ፓትሪአርክና ደጋፊዎቻቸውን ሊያስደስት ይገባል። ለሥልጣን እንዳይባል- ሥልጣን ከቀረ ዓመታት አልፈዋል። ደግሞስ ለምንኩስና መሐላ፡- ለጵጵስና መሐላ፡- ለፐትርክናም መሐላ መገዛት ሰው በሕይወት እያለ መሰለኝ። “ኹለት ዓይን ኖሮህ ከ…አንድ ዓይን ኖሮህ ብ…”ን ማስታወስስ አይጠቅም ይኾን?

ባለንባቸው ጊዜና ኹናቴ ርሳቸውና ደጋፊዎቻቸው የፈለጉት እንደማይገኝ የታወቀ ሲኾን ካልኾነ ብሎ ቤ. ክርስቲያናችንን ክፉ አደጋ ላይ መጣል ማንን ለመጥቀም ማንንስ ለመጉዳት ነው? ለርሳቸውም ስምና ክብር ማሰብ የለብንም? አኹን ባለንበት የእምነት ብቃት ወቅት "ተራራውን ተነስትህ..." ማለት እንችላለን? እንግዲያውማ እዚህ ደረጃ እስክንመለስ እንኳን

## "አንተ ታውቃለህ፡- ማረን ፡- ምራን!"

ብንለው አይሻልም?

**የዕርቅ ጉባኤ አባላት ሆይ፡-** እንደምታውቁት ከላይ ሕገ መንግሥት ተብዬው ጸደቀ በተባለብት ግብዣ ላይ ምድራውያን ኃያላን ኢትዮጵያችንን **"በቁጥጥራቸው ውስጥ ለማስገባት"** ካጠመዱባት ወጥመዶች የበለጠ የጎዳን በሲኖዶስ ስም በተለያዩ አስተዳዳሪዎች ምክንያት የተፈጠሩት ችግሮች መኾናቸውን የሲኖዶሶቹ አባላት አልታያቸው ከኾነ እባካችሁ ጊዜ ወስዳችሁ በወንጌላውያን ስም ቤተክርስቲያናችን አሥራ ስምንት ሚሊዮን ልጆችዋን ማጣትዋን አበክራችሁ አስረዱቸው።/ አርዷቸው። በየገጠር ቤ.ክርስቲያናት ሚደርሰውንም...
በተለይ አዲስ አበባ ውስጥ ግብረ ሰዶም (በሴቶችም መኻል) በይፋ በሚያሳፍር ኹናቴ መኪያሄዱን አዎን "መኪያሄዱን" የሲኖዶስ አባላት በተለይ የአዲስ አበባዎቹ አናውቅም ይሉ ይኾን? ከመንጋቸው ፈጽመው ርቀዋል ማለት ነዋ። ይህም አስጊና አሳፋሪ ነው። አቅመ አዳምና ሄዋን ባደረሱት ብቻ ሳይኾን ከ፲፫-፲፰ እድሜ ውስጥ ያሉትን ጨቅላዎች ወላጆች ት/ቤት ብለው ልከው ሲመለስት ልጆቹ መቀመጥ ሲያቅታቸውና ሲመረመሩ ወላጆች መርዷቸውን ያገኛሉ። ለማን አቤት ይበሉ? የወላጆች ምርጫ ልጆቻቸውን ከሃብታም አገር ጎብኚዎች መስተንግዶነት ለማዳን ደኅና ት/ቤት ናደን አልያም እቤት ማስተማር መኾኑንስ??!!

# የሰዶም እጣ በምንኛ ከፍቶ ይመጣብን ይኾን!!! ወንጀለኞቹ ኹሉም የሃይማኖቶች ድርጅቶችና የኹሉም ምእመናን መኾናችንን ዐውቀንና አምነን 'እግዚኦ!' እንበል እንደእየምነታችን። አለበለዚያ አኹን ከወደቅንበት አዘቅት አንጥሮጦስ ብንወርድ ከራሳችን በስተቀር የምንወቅሰው የለም። እንወቅበት!!! ከመቅረት መዘግየትም ይኹን!

ከውንጌለኞች መለየት የባሰ ድግሞ እውስጣችን አለ። "የባሰ??" የሚል ካለ መልሱ አዎን ነው። በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ስድስት/ሰባት ደማሚቶች ተጠምደዋል። ከነዚህ ውስጥ አንዱ ሊፈነዳ ደርሷል። እስካሁን ያልፈነዳውም በአጥማጆቹ ውስጥ ጥሩ የቤተክርስቲያኗና የአገሪቱ ልጆች በመኖራቸው ብቻ ነው። ስለዚህ አኹን የቤተክርስቲያናችን አስተዳዳሪዎች ኹሉ፡- የሰማዩን አላውቅም ከትውልድ እስከትውልድ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ቢተክርስቲያን ያጠፉት ተብላችሁ "ሱልጣን ኢብራሂም አሰብን የሸጠ!" ተብሎ በታሪክ መዛግብት ውስጥ ፎቶግራፉ እየታየ እንዳለው እንዳትኾኑ እባካችሁ ለሥላሴ ተገዙ።

ልጅ ኢያሱ ሃይማኖት ለመለወጣቸው ማስረጃ ተብሎ ፎቶግራፍ በቀረበ ጊዜ " እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ የሥላሴ ባሪያ የኾንህ ወደዚህ...የኾንህ ወደዚያ!" ያሉት እንዳይመጣ እንጠንቀቅ።

## ሱባኤ እንግባ ያልሁትም ለዚሁም ጭምር ነው

## *ተማጽኗችን*

## *"አንተ ታውቃለህና ማረን - ምራን ይኹን!!!"*

## ቢኾን አይሻልም?

*ማንንም ለማስቀየም፡- ማንንም ለማሳዘን ሳይኾን ቤተክርስቲያናችንን ለማዳን በመሞከር ያስቀየምሁት ካለ ይቅርታ!*

*ሙስሊም ወንድም እህቶቼ ሆይ፡-*

ከላይ እንደጠቀስሁት ኢትዮጵያችንን ቁጥጥራቸው ውስጥ ለማስገባት የእኛን ቤተክርስቲያን በወንጌላውያን የእናንተን በአክራሪዎች ሊመርዙ** መወሰናቸውን ላስታውሳችሁ። (ሊመርዙ ስል በነርሱ ምኞትና ዕቅድ እንጂ ይህ ጸሐፊ ቀ.ኃ.ሥ " ሃይማኖት የግል አገር የጋራ!" ያሉትን ተቀባይ መኾኑን እንድትረዱለት አደራ ይላል! አክራሪ የሚባል ነገር ግን በማንኛውም ነገርና ጉዳይ አደገኛ መኾኑን ያምናል።

በእኛ በኩል የኾነውን ከላይ ነካ ነካ አድርጌዋለሁ። ከድፍረት እንዳይቆጠርብኝ በናንተ ላይ የተፈጸመውን ለናንተው ስተው ሀዘናችሁ ሀዘኔ፡- ችግራችሁ ችግሬ እንባችሁ እንባዬ ሳይኾን ቀርቶ አይደለም፤፡በአንዳችን ላይ የመጣው ሌላችንን አያስተርፈንምና እናንተም ለዚሁ የጸሎት ጥሪ አብራችሁን ኹናችሁ፡- ወገን ከወገን ከመበላላትና አገርንም ለማዳን አብረን እንኹን። እግዚአብሔር ይስማን።

*ይህ ጥሪ ወንጌላውያን ወንድሞቻችንን እንደሚጨምር መናገር ባያሻም እንኳን ለማጥበቅ ያህል አደራ።*

# አፈጻጸም

የአስታራቂ ጉባኤው ህሳቤን ተቀባይ እንደሚኾን (በሚመስለው አጠንክሮ) በማመን ለአፈጻጸም ይረዳ ከኾነ አንዳንድ ልበል፡-

እናንተ ባጠናከራችሁት መልክ ተቀባይነት ካገኘ! እሰየው ሥላሴ የመረጡልንን ይስጡን። ሲኖዶሶቹ፡- ወይም ከሲኖዶሶቹ አንዱ አልቀበልም ቢል ያልተቀበለውን ወገንና ምክንያት ለሕዝብ በጋዜጣዊ መግለጫ ስታስረዱ ለአገር ለወገን ለጸሎት ሕዝብን ለመጥራት የሚከለክላችሁ ያለ አይመስለኝም። እናንተ ቀን ወስናችሁ ሱባኤ ብትጠሩ እንድንድን መልካም አስተዋጽኦ እንደምታደርጉ አልጠርጠርም። የሥላሴ መሣሪያዎችም መኾናችሁ ይኾናልና፡- አታቃልሉት ስል በማክበር ነው። ገጠሬዎችና ገዳማት ይተባበራሉም ብዬ አምናለሁ።

*ለሕዝብ ስትገልጡ ስል፡-

በቀደምት መግለጫው ላይ በተሳታፊነት ቢጋበዙ ይጠቅማል የምለው

- ሃይማኖታዊ ድርጅቶችን በሙሉ
- በአገራችን ጉዳይ የፖቲካ ፓርቲዎች
- ሰባዊ ድርጅቶች
- ሕዝባዊ ድርጅቶች
- ውዘተ

ፖለቲካ ፓርቲዎች ስል ግራየሚጋቡ ሊኖሩ ስለሚችሉ፡- ባጭሩ ላስረዳ። በቤተክርስቲያናችን ለችግራችን መንሰኤው ፬ኛውን ፓትሪአርክ ማስነሳቱ ስለኾነ የፖለቲካ ችግር ነው። ስለዚህም ፖለቲከኞች በፈንታቸው ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጥሩ ብቻ ሳይኾን አኹንም ተከታዮቻቸው ለጸሎቱ ተባባሪነት እንዲያስታውቁም ነው፤ ፡

## መሣሪያው፡-

አገር ውስጥ የሚሰሙትን

- የእሳትን ቲ.ቪና ሬዲዮ
- የአሜሪካንን ድምጽ "
- የጀርመንን "
- ፍኖተ ዴሞክራሲን (ኢሓአፓ) "

- ሌሎችም ካሉና የየአካባቢዎች ሬዲዮ ጣቢያዎችና ዘመናዊ የሕዝብ መገናኛዎች (ድረ-ገጾች)
- የወዳጆች መነጋገሪያ (ፓል ታልክ ሩምስ)

ተዳርሰው ወገንን እንዲቀሰቅሱ መሞከር ይጥቅም ይመስለኛል። የሃይማኖት ወንድም እህቶቼ ሆይ ችግራችንን ለመፍታት ስንጥር ፡-

ማቴ.ም ፳፫ ቁ ፳፮ን እናጢን፡
"እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፡ በውጪ አምረው የሚታዩ በውስጥ ግን የሙታን ርኩሰትም ኹሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትምስሉ ወዮላችሁ፡…"

ወስብሐት ለእግዚአብሔር !